# የጎንደር ሕብረት

## ይድረስ ለጎንደር ሕዝብ

## ልዩ መልዕክት ቁ. 5

የጎንደር ክፍለ ሃገር በዚህ በያዝነው ዘመን የትግራይ ነጻ አውጭ ግንባር በተባለ ቡድን የጥቃት ሰለባ መሆኑን በተደጋጋሚ ተጽፏል፣ ነገር ግን ግፍ እና በደሉ ሰሚ ካጣ ብዙ ዓመታትን አስቆጥሯል። አሁንም መከራው እና ሰቆቃው ያላቆመው የጎንደር፤ የወልቃይት እና ጠገዴ፤ እንዲሁም የጠለምት ህዝብ በቁሙ እዬተቀበረ ነው። የዛሬው መግለጫችን የሚያተኩረው ለሚመለከታቸው የማህበረሰብ አካላት ሁሉ መልዕክታችን በማስተላፍ ነው።

ክፍለ ሃገሩ ካሉት ሰባት አውራጃወች የወገራና የደባርቅ አውራጃ ወረዳዎች አብዛኛወቹ በጉልበት ወደ ትግራይ አስተዳደር እንዲጠቃለሉ በመደረጉ ኗሪው ህዝብ የወገን ያለህ እያለ ነው። የጎንደር ህዝብ ትጥቅ የለውምና መሬቱን ፈርቶ ይሰጣል በሚል ሥሌት አሁንም እንደገና የጭልጋን እና የጎንደር ዙሪያ ወረዳዎችን ለመቆጣጠር የትግራይ ህዝብ ነጻ አውጭ ግንባር ከነበሩት አጥፊ እና ጠብ ጫሪ ሚሊሻዎቹ በተጨማሪ፤ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ አዲስ ሚሊሻዎችን በማሰልጠን የወልቃይት ወገኖቻችንን የጎንደሬነት ጥያቄም ሆነ የይሥሙላ ምርጫን በግፍ ለማፈን ተጨማሪ ዝግጅት በማድረግ ላይ እንዳለ በተለያዩ የዜና አውታሮች ተዘግቧል።

መልክታችን አንድ እና አንድ ነው። ድንበራችን ተከዜ ነው! እያለ ያለው  የመላው የሰባቱ አውራጃወች የጎንደር ሕህዝ ድምጽ መከበር አለበት ። የወያኔ ወረዳዎችን  የመንጠቅ በሽታ ጎንደርን ብሎም ኢትዮጵያን የመበታተን ዘመቻ በመሆኑ ይህንን ሴራ ለመቀልበስ በዬአውራጃው እና በየወረዳው ሁሉም በየአካባዊ መሪውን መርጠ ለመብቱና ለድንበሩ ዘብ የመቆም ታሪካዊ ግዴታ አለበት።

ባለፉት 24 ዓመታት ልዩ የጎንደር እምብርት የሆኑትን ወረዳዎች ያለ ፍላጎት ወደ ትግራይ በመከለል፤ ይህን የሚቃወሙ ኗሪዎችን ድብዛ  በማጥፋት፤ የወያኔን የግዛት የበላይነት አጠናክረዋል። በያዝነው ዓመት ደግሞ ወደ አርማጭሆ እና መተማ ወረዳዎች የይገባናል ጥያቄ አንስተው ወረራ ለማካሄድ በዝግጅት ተጠምደዋል። ይህ ደግሞ፤ የወያኔ ኢትዮጵያን የማጥፋት የመጀመሪያው አጀንዳ በጎንደር ለማጠናቀቅ የመጨረሻው ሙከራ ነው።  በመሆኑም፤ "አፍንጫ ሲመታ አይን ያለቅሳል" ነውና ጎንደር ላይ ጥቃት ሲደርስ የኢትዮጵያ ህዝብ በትዝብት መመልከት የለበትም የሚል ሙሉ እምነት አለን። ዛሬ ጎንደር ከተጠቃ ነገ ደግሞ የሌላው እጣ ፈንታ ምን እንደሚሆን መገመት አያዳግትም ።

**የጎንደር ህዝብ ሆይ!**

በክፍለ ሃገራችን አስቸጋሪ የሆነ የታሪክ አጋጣሚ ተከስቷል። በአሁኑ ዘመን በውስጥም በውጭም የምንኖር የጎንደር ተወላጆች ታይቶ ተሰምቶ በማይታወቅ ሁኔታ ትውልድ አገራችን ላይ እየደረሰ ያለው ጥቃት እጅግ አሳስቦናል። ስለሆነም የህዝባችን ትግል ደጀን ለመሆን የጎንደር ህብረት በሚል ስያሜ ተደራጅተን ከህዝባችን ጎን ለመቆም በእንቅስቃሴ ላይ መሆናችንን ባለፈ ወር አስታውቀናል፤ ይህም በጎንደር ላይ እየደረሰ ያለዉን ጥቃት ተባብረን ለመመከት ከብዙ ተከታታይ ዉይይት በኋላ ሙሉ በሙሉ ታምኖበት የተወሰነ የአብሮነት ጥሪ ነዉ።

የጎንደር ህብረት ዋና ዓላማ፤ የተለያዩ ጎሳዎችን በውስጧ አቅፋ በምያዝ ለአጠቃላይ የአንድነታችን ምሳሌ በመሆን የምትታወቀውን ክ/ሀገራችን ታሪክ ለማስጠበቅ በመሬት መሥፋፋት አጉል ቅዠት ሰለባ እና አደጋ ላይ ያለዉን ህዝብ መታደግና ዳር ደንበሩን ለማስከበር የሚያደርገዉን ትግል ማገዝ ነዉ። በጉልበት የተወሰዱ የጠለምት፤ የወልቃይት ጠገዴ የሁመራ ወረዳወች ወደ እናት ጎንድር አስተዳደር ለማስመለስ በሚቻለዉ ሁሉ መተባበር እና በክፍለ ሃገራችን ፍጹም በዘር መከፋፈል እንዳይኖር ነጻነት፤ ፍትህና እኩልነት እንዲሰፍን ተባብረን ለመስራት ነዉ። እንዲሁም መሬቱን እዬተቀማ ምንንቱን እያጣ ላለዉ ህዝባችን ድምጽ ለመሆን ተደራጅተን የዘር ማጥፋት ወንጀልን ለዓለም ህብረተሰብ ለማሰማት ዋና ዓላማችን ይሆናል። ጎንደር ሕብረት (ጎሕ) እራስን ለመከላከል የጎንደር ጭንቅ የወለደዉ ድርጅታችን ነዉ። ለድርጅቱ መፈጠር ብዙ ምክንያቶች አሉ። በአጠቃላይ ግን የጎንደር ክፍለ ሃገር መሬቱን መቀማት ብቻ ሳይሆን ትዉልዱንም እያጣ ነዉ። በወያኔ ዘመን በጎንደር የደረሰዉ ድፍረት፤ ዉርደት በክፍለ ሃገሩ ታሪክ ካሁን በፊት በፍጹም አልታየም። በአማራዉ ክልል በግምት 5 ሚሊዮን ከጠፋዉ የሰዉ ህይወት አብዛኛዉ በዚሁ ክፍለ ሃገር የደረሰ ጥፋት ሲሆን፤ በተለይም ተከዜን ተሻግሮ ወያኔ በወረራቸዉ ወረዳዎች በደረሰ ጭፍጨፋ እና በአስደንጋጭ ሁኔታ በተደረገ የዘር ማጥፋት ወንጀል ምክንያት ነው። የጎንደር ህዝብ ብዙ ግፍና መከራ በህወሃት ተፈጽሞበታል። ወደፊትም ፈታኝ ሁኔታወች ተደቅነዉበታል። በዚህ አስቸጋሪ የመከራ ዘመን የእርስ በእርስ ግጭት በጎንደሬ መካከል ፍጹም የተወገዘ ነዉ፤ መለስተኛ ችግር ቢኖርም ለክፍለሃገራችን ደህንነትና አንድነት ሲባል ይቅር ተባብለን እንደ አባቶቻችን በሽማግሌ እንፈታዋለን።

## ለጎንደር ተወላጅ ሁሉ

የምርምር እና የጠበብትነት ነጻነት ያጣኸዉ የጎንደር ሊቃዉንት፤ ምሁራን፤ ከንቱ በሆነ የትምህርት ሥርዓት የዉሸት ዲግሪ እዬሸመቱ መሪ ነን በሚሉ ሚኒስተሮች የተበደልከዉ ተማሪ እና አስተማሪ፤ የመሬት ባለቤትነትክን የተነጠከዉ ሰፊዉ አራሽ ገበሬ ፤ በስርዓቱ የመድሎ ግብር የተጨፈለከዉ የትንሽ እና የትልቅ ባለ ሃብት ነጋዴ፤ በሥራ አጥነት የናወዝከዉ የወደፊት አገር

ተረካቢ የሆንከው ወጣት ትውልድ፤ የስልጣን ማራዘሚያ ሁነህ በሙስና የተዘፈቁ መሪዎች መጠቀሚያ የሆንከው ጭቁኑ መለዮ ለባሽ የኢትዮጵያ ሰራዊት ሆይ! ጎንደር በጎንደርነቱ ካልቀጠለ ያንተ መኖር፤ ያንተ ምንነት ወይም ኢትዮጵያዊነት ከንቱ ነው እና የጥቃቱን ዘመቻ እዬሰማህ ከአፍ ወደ እጅ በሆነ ጥቅማጥቅም ተዘናግተህ የትውልድ አገርህ ሉዓላዊነት እንዳልነበረ ሲሆን አድፍጠህ ታዛቢ እንዳትሆን አደራ እንላለን፤ የድርሻህን በምትችለሁ ሁሉ ተወጣ።

በተለይ በአሁኑ ወቅት ጎንደርን በዘር በመፈረጅ አማራ እና ቅማንት ብሎ በንዑሥ ክልል ለመከፋፈል የሚደረገው ህዝብን የማለያየት ሴራ "ከእንቅርት ላይ ጀሮ ደግፍ" እንዲሉ ነው እና፤ የሁለቱም ወገን ምሁራን የውይይት መድረክ ከፍታችሁ የሊቅነት ልሳናችሁ እና የታሪክ ጽሁፍ ብዕራችሁን በማንሳት ተግታችሁ መሥራት  አስፈላጊ ነው የሚል እምነት አለን። በኛ በኩል ለዚህ የተቀደሰ የሰላም ጥሪ፤ አቅማችን በፈቀደ መጠን አስፈላጊውን እርዳታ ለማድረግ ዝግጁ ነን።

ከዚህ በመለስ ግን እጅግ ያሳዘነንን ጉዳይ ሳንጠቅስ አናልፍም። ይህም ለጎንደር አንድነት እና ብልጽግና ተስፋችን  የሆኑት ብርቅዬ የጎንደር አዋቂ ልጆች፤ የተከበሩ ዶክተር ማለደ ማሩ፤ ክቡር አምባሳደር ዘመነ ካሰኝ፤ የተከበሩ ፕሮፌሰር ይግዛው ከበደ፤ የተከበሩ መምህር ምስጋናዉ ፈንቅለዉ፥ የተከበሩ መምህር እንደሻዉ ቦጋለ እና የመሳሰሉት ምሁራን፤ የቅማንትን በራስ አስተዳደር የማስከለል የአንቀጽ 39 አካል የሆነውን ጥያቄ አንስተው ለማስፈጸም  ዋነኛ ተዋናኝ መሆናቸዉን ስንሰማ እጅግ ማመን አቅቶናል። ምንም እንኳ ገዥዉ መንግስት ባመጣዉ ዘርን መሰረት ባደረገ  ፖሊሲ ተገፋፍተው ቢሰሩትም፤ አሁንም ሥህተቱ ታርሞ በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ምክክር ተደርጎ የሁላችን የአብሮነት እና ምንነት በአንድነት እና በፍቅር እንዲቀጥል በአክብሮት እንጠይቃለን። የጎንደርን የዘመናት ዉህደት ታሪክ በዘር መከፋፈል ፍጹም የማይሆን ጉዳይ ነዉ፤ ይህ ነገር ከተከሰተም እጅግ ከባድ ጉዳት የሚያደርስ አደጋ ነው።

ክቡራን የጎንደር ተወላጆች፥ የጎንደር መልካም ታሪክ እና ምንነት በሁሉም ጎንደሬ ነገዶች የተከናወነ የአንድነት ጸጋችን  በመሆኑ ሁሉም በነጻነት በፍቅር ተከባብረዉ የሚኖሩባት ጎንደር መኖር ለሁላችን የጋራ  ዘላቂ ጠቀሜታ አለዉ። ስለሆነም፤ ዲሞክራሲያዊ፤ እኩልነት እና ፍትህ በመላዋ ጎንደር እንዲሁም  ለሁሉም ኢትዮጵያውን እንዲሰፍን በአንድነት ጠንክረን በመታገል ጎንደርን የመፍትሄው አካል እንድትሆን መጣር። ይህም ያልተለመደ ባህሪያችን አይደለም። የጎንደር ህዝብ ዳር ድንበሩን ለዘመናት ደሙን አፍሶ አጥንቱን ከስክሶ ክፍለ ሃገሩን ብሎም ከሁሉም ጋር በጋራ ቅድስት አገር ኢትዮጵያን አስከብሮ ኑሯል። ዲሞክራሲያዊ መብቱ ግን እንደማንኛዉም  ኢትዮጵያዊ አልተከበረም። ተበድሎ የቁም ሞትን እየሞተ ብዙ አመታትን አሳልፏል። አሁን ግን ጭራሽ ህልውናውን ለማጥፋት አገር በቀል ሃይል ተነስቶበታል። ይህንን ፀረ ጎንደር የመስፋፋት አባዜ የተጠናወተዉን ወራሪ ሃይል በሕብረት ተነስተን መቋቋም  አስፈላጊ ሁኖ

አግኝተነዋል። እናም፤ በውስጥም በውጭው ዓለም የምትኖሩ የጎንደር ተወላጆች በያላችሁበት ተደራጅታችሁ ተባብረን እና ተመካክረን ድንበሩ ተከዜ የሆነውን ጎንደርን ለማስከበር አስፈላጊ በሆነው ሁሉ በመታገል የተለምዶ ታሪካችን የሆነውን አንድነታችን እንድናሳይ ጥሪያችን እናቀርባለን።

ትግላችን በአጠቃላይ የኢትዮጵያን ህዝብ ድጋፍ እና ትብብር ይጠይቃል። ለዚህ ደግሞ ጎረቤት እንዲደርሥልን፤ እንደ ባለቤት መጨኸን ይጠይቃል። ስለሆነም፤ መላው የኢትዮጵያ ህዝ በጎንደር ክፍለ ሃገር እዬተፈጸመ ያለውን ግፍ በጥብቅ ያወግዛል የሚል እምነት አለን። ከሁሉም የበለጠ አሳሳቢ  ጉዳይ ደግሞ የጎንደርን ህዝብ እርስ በእርስ የማጋጨት ሙከራ ነው። ይህንን ቤተሰብ ከቤተሰብ የማዳማት እርኩስ ተግባር ሰፊው የጎንደር ህዝብ አይቀበለውም፤ ፍቅሩና አብሮነቱ አሸናፊ ሆኖ ይህን ዘመን ያልፋል።

## ለሃይማኖት አባቶች

በጎንደር ዙሪይ እና በመላ ኢትዮጵያ የምትኖሩ የሃይማኖት አባቶች፤ የህዝብ ሰላም እና መረጋጋት እንዲኖር፤ የእርስበስ ግጭትን እንዲወገድ ጸልዩ። የህዝብን በደል እና ጭሆት ሰምታችሁ ዝም አትበሉ። በወልቃይት ጠገዴ የሚካሄደውን የዘር ማጥፋት ዘመቻ  ማውገዝ ሃይማኖታዊ ግዴታችሁ መሆኑን እናምናለን፤ ዘረኝነት ከንቱ እንደሆነ አስተምሩ። የቅማንትና የአማራን ህዝብ በንዑሥ ክልል የሚከፋፍል አዲስ የዘር ድንበር በጎንደር ህዝብ መካከል ሊፈጥሩ  ሲሯሯጡ በቅድሚያ የተሳሳተ እኩይ ተግባር መሆኑን መቃወም ያባቶች ሥራ መሆን አለበት የሚል ሙሉ እምነት አለን። አላፊ ለሆነ ዘመን እና ጊዜ፤ ባለስልጣኖችን ላለመገሰጽ የሰላም እና የፍቅር አባትነታችሁን ሥራ ዘንግታችሁ ልሳናችሁ ይዘጋል የሚል ዕምነት የለንም። ግን ጊዜው ሳይመሽ ከናንተ ከአባቶች የሰላም እና የአንድነትን መልክዕት እንድታስተላልፉ እንጥይቃለን። በአጠቃላይ በመላው ጎንደር ያሉ አድባራት፣ ካህናት እና ምዕመናን ለክፍለ ሃገራችን አንድነት ጸንታችሁ እንድትቆሙ እንማጸናለን።

## የትግራይ ህዝብ ሆይ!

እንደሚታወቀው በብዙ የጉርብትና ዘመናችን ታሪክ የጎንደር እና የትግራይ ህዝብ ለብዙ ሺህ ዓመታት ጥሩ ጎረቤት ሁኖ ኑሯል። የደስታም ሆነ የመከራ ኢትዮጵያዊነቱን በጋራ ተባብሮ፤ በሰው ሰራሽም ሆነ የተፈጥሮ ችግርን ተቋቁሞ በፍቅር ኑሯል። የጎንደር እና የትግራይ  ድንበር የተከዜ ወንዝ እንደሆነ ታውቃለህ። የሁለቱ ክፍለ ሃገራት ተወላጆች በየትም ቦታ ተንቀሳቅሰው በሰላም ሰርተው የመኖር መብታቸው የተጠበቀ እንደሆነ እናምናለን። የትግራይ ህዝብም ይህንን እውነታ አይረሣውም። ነገር ግን በዓለፉት 24 ዓመታት መነሻውን  ከትግራይ ያደረገ የትግራይ ህዝብ ነጻ

**አውጭ ግንባር ብሎ እራሱን የሚጠራ ድርጅት የጎንደርን ወረዳዎች በጉልበት በመንጠቅ ላይ ይገኛል። የአዲስ አበባባን ቤተ መንግስት የስልጣን ተገን አድርጎ በትግራይ እና በጎንደር ህዝብ መካከል ጦርነት ለመክፈት እና ኢትዮጵያዊ ወንድማማችነታችን በደም ለማቅለም፤ ያለ ችግር ታሪካዊ ድንበራችን ጠብቀን በጋር እንኖር የነበረውን በክልል ይገባኛል ተንኮል ግንኙነታችን እያበላሸ ይገኛል። በመፈቃቀድ እና በሰላማዊ መንገድ ኑሮን በጎንደር መሬት ማስቀጠል የሚቻል እና የነበረ ነው። ይህም ከጥንት አባቶች የተወረሰ የህዝባዊ ፍቅር ሰንሰለት መቀጠል አለበት። ማንም ኢትዮጵያዊ በፈለገው ቦታ በነጻነት መኖር የኢትዮጵያዊነት መሰረት ነውና፤ በሁሉም ክፍለ ሃገራት ሰርቶ ባለሃብት መሆን እንደሚችል የጎንደር ህዝብ ሙሉ ዕምነት ነው። ለዘመናት በአራቱ ማዕዘን የመጡ ነገዶች ሁሉ የሚኖሩባት ሃገር መሆኗን በመልካም ሥም የታተመዉ የጎንደር የታሪክ አሻራ የሚያረጋግጠዉም ይህንን እዉነታ ነዉ። ይህ መልካም ታሪካዊ የሆነ ህዝባዊ ግንኙነት በእኩይ ታጣቂ ወያኔዎች እንዳይበላሽ፤ ችግሩንም ለማስወገድ የትግራይ ህዝብ በስሙ የሚነግዱ በሙስና የተዘፈቁ ገዥውዎችን የጥፋት ተልኮ እንዳይከተል በጥብቅ መልክታችን እናስተላልፋለን። በቃ! አቁሙ ሊላቸዉም ይገባል። ወደፊት ወያኔ በሚያካሂደዉ የወስን ማስፋፋት እና የመሬት ዘረፋ ዘመቻ፤ ታሪክን ያላገናዘበ ጉልበት እና ሃይልን መሰረት ያደረገ በመሆኑ በትግራይ ስም ህወሃት በሚከፍተዉ የግዛት መስፋፋት ጦርነት ለመሳተፍ ፈቃደኛ እንዳትሆኑ በጥብቅ እንጠይቃለን። ተከዜን ተሻግሮ መቀሌ ላለዉ ህወሓት ግብር የማስከፈሉ የግፍ አገዛዝ በአስቸኳይ ይቁም!**

**የጎንደር ሕብረት**

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!!**